በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን ግንቦት 09 2015
Date
ቁጥር 3.1/ 425/15
Ref.No

በአባሪ ለተዘረዘሩት በሙሉ

በያሉበት፣

ጉዳዩ፡- የተሻሻለውን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1287/2015 እና የተደረጉ ማሻሻያዎችን ስለማሳወቅ ይመለከታል፤

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ከየካቲት 5/2012 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን፤ ይህ አዋጅ የታክሱን መሰረት በማስፋትና የታክሱን አስተዳደር ስርዓት በመቀየር ከፍተኛ ጠቀሜታን ያስገኘ ሲሆን ከታክሱ የሚሰበሰበው ገቢ በተደረገው ማሻሻያ ከፍተኛ እድገት ያሳየና ሪፎርሙ ውጤታማ መሆኑን ያመለክታል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ባካሄደው 15ኛ መደበኛ ጉባዔው በአዋጁ ላይ የቀረቡ የማሻሻያዎች ታሳቢዎች ማለትም፡-

1. ተደራራቢ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ምርቶች ላይ ማሻሻያ ለማድረግ፣
2. በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ላይ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል ለማድረግ፣
3. የኤክሳይዝ ታክስ ተጥሎባቸው የነበሩት አንዳንድ ምርቶች ላይ ታክሱን ለማንሳት፣ እንዲሁም
4. በአስተዳደር ምክንያት የተደረጉ ማስተካከያዎችን እና የማሻሻያውን ዋና ዋና ምክንያቶች ከመረመረ በኋላ የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1287/2015 ማጽደቁን እና አዋጁ ከፀደቀበት ከሚያዚያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/955 በ 26/08/2015 ዓ/ም በፃፈው ደብዳቤ ለመ/ቤታችን አሳውቆናል፡፡

ስለዚህ የአዋጁ ማሻሻያ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተላከውን በምክር ቤቱ የፀደቀውን የአዋጁን ማሻሻያ እና አዲስ የተካተተውና የተሻሻሉትን (ተሽከርካሪ በዝርዝር ከአዋጁ እንዲታይ ሳይጨምር) ለአፈጻጸም እንዲረዳ ለመነሻ የተዘጋጀውን ሠንጠረዥ ጭምር በኢሜል አባሪ ተደርጎ የተላከላችሁ ስለሆነ በተሻሻለው ህግ አግባብ እንዲፈጸም የስራ ክፍሉ እና የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሁሉ እንዲያውቁት፣ ለታክስ

የበለፀገች ኢትዮጵያ!
Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

ተመዝጋቢዎችም በቅ/ጽ/ቤቱ መረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች በመጠቀም መረጃው እንዲኖራቸው እንዲደረግና አፈጻጸሙም ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግበት እያሳሰብን፣ ቀደም ሲል ሲከፈልባቸው የነበሩ ምርቶች እና ከታክሱ ነጻ የተደረጉት እስከአሁን የሰበሰቡትን በትክክል ማስገባታቸውን እንዲረጋገጥ ሆኖ ሰርተፍኬቱን እንዲመልሱ በጽሑፍ እንዲገለጽላቸው እናስገነዝባለን፡፡

የኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬትም የተሻሻለውን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1287/2015 እና የተደረጉ ማሻሻያዎችን የንግዱ ማህበረሰብ እንዲያውቀው ባሉት የመገናኛ ብዙኃን መልእክት እንዲተላለፍ የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ ተመዝግቧል፡፡

ከሰላምታ ጋር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

አይነኸ አባይ
የታክስ ማስታወቅ
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

- ለሚኒስትር ፅ/ቤት
- ለታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለታክስ ስርዓት ዘርፍ
- ለታክስ ከፋዮች ምዝገባ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ስርዓት ማጣጣምና ክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስና ጉምሩክ ጉዳዮች ማብራሪያ፣ ምክርና ድጋፍ ዳይሬክተሬት
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክተሬት
- የኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

**በአባሪ የተዘረዘሩት**

ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለምስራቅ አ/አ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት

ለምዕራብ አ/አ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት

ለሰሜን ምዕራብ አ/አ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢ.ዎች ቢ.ሮ

**አዲስ አበባ**

ለባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት /ባህር ዳር/

ለአዳማ ቅ/ፅ/ቤት/አዳማ/

ለመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት /መቀሌ/

ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/

ለሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት /ሀዋሳ/

ለጅማ ቅ/ፅ/ቤት /ጅማ/

ለድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት /ድሬዳዋ/

አዲስ የተጨመሩ

| የታሪፍ ቁጥር | የእቃው አይነት | የማስከፈያ ምጣኔ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| | የሞባይል አገልግሎቶች(ኢንተርኔት፣ የድምፅና የፅሁፍ መልዕክት) ፣ የገመድ አልባ ስልክ አገልግሎት፣ የገመድም ሆነ ገመድ አልባ የኢንተርኔት አገልግሎቶች | 5% | |

የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋቸው የቀነሰ

| የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | የበፊቱ ማስከፈ.ያ ምጣኔ | አዲሱ ማስከፈ.ያ ምጣኔ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ምድብ 15 ላይ የተዘረዘሩት | ለምግብነት የተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም የሳቹሬትድ ቅባት መጠኑን ከተለጠፈበት መግለጫ ላይ ለማወቅ የማይቻል የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብና ዘይት እና የእነዚህ ተዋፅዖ ውጤቶች፤ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሀይድሮጅን የተጨመረበት የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብና ዘይት | 30%<br>40% | 30% | |
| 17.01 | ስኳር ለህክምና ከሚውለው በስተቀር | 20% | 10% | |
| 1704.1000 | ማስቲካ | 20% | 10% | |
| ከ1704.90 እስከ 1806.90 | በቀጥታ ለምግብነት እንዲውል የተዘጋጀ ቸኮሌት እና ጣፋጭ ከረሜላዎች | 20% | 10% | |
| 2207.10 እና 2208.9090 | ባህሪው ያልተለወጠ ኢቴል አልኮል | 60% | 10% | |
| 2501.0010 | ጨው | 25% | 10% | |
| በምዕራፍ 27 የሚመደቡ | ኬሮሲን፣ ቤንዚን እና ናፍጣ ነዳጆች | 30% | 15% | |
| ምዕራፍ 50 እና እስከ 63 ከ57 በስተቀር | ጨርቅና ልብስ | 8% | 5% | |
| ምዕራፍ 57 | ምንጣፎች፣ ከጨርቃ ጨርቅ የተሰሩ የወለል መሸፈኛዎች | 30% | 15% | |
| ከ8701.10 እስከ 8711.90 ድረስ ያለው በተሻሻለው አዋጅ አባሪው ላይ ባለው መሰረት | | | | |

በአዲሱ አዋጅ ነፃ የሆኑ /የማይመለከታቸው

| ታሪፍ ቁጥር | የእቃው አይነት | ነባሩ ማስከፈያ መጣኔ | በአዲሱ |
|---|---|---|---|
| 8521.1000 እስከ 8528.7300 | ቪድዮ መቅረጫ ወይም ማባዣ መሳሪያዎች፣ የቴሌቪዥን ስርጭት መቀበያዎች፣ ፎቶ ወይም ቪድዮ ካሜራ | 10% | ነፃ |
| ከ8701.10 እስከ 8711.90 ድረስ ያለው በተሻሻለው አዋጅ አባሪው ላይ ባለው መሰረት | | | |

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. 2/ገ/ህ/2/955

ቀን / Date 26/08/2015

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ባካሄደው 15ኛ መደበኛ ጉባዔው በተዘጋጀው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ በስፋት ከተወያየ በኃላ ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 1287/2015 ሆኖ በሥራ ላይ እንዲውል አፅድቆታል።

ስለዚህ የአዋጁ ማሻሻያ በምክር ቤቱ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እያሳሰብን ለአፈፃፀም እንዲያመች በም/ቤቱ የፀደቀውን የአዋጁን ማሻሻያ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

አዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፣
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

አዋጅ ቁጥር ________/2015

# የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ወደአገር በሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎች እና አንዳንድ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን እጅግ በጣም ከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በልዩ ሁኔታ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ሰዎች እና ድርጅቶች በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ጭምር ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው እንዲያስገቡ መፍቀድ ተገቢ ባለመሆኑ፤

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልበት ማድረግ መንግሥት ለሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች የሚውል ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ ስለታመነበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (11) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (ማሻሻያ) ቁጥር _____" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2020 (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፤

1. ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (22) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (23)፣ (24) እና (25) ተጨምረው በነባሩ ከንዑስ አንቀጽ (23)-(34) የሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (26)-(37) ተደርገው ተሸጋሽገዋል፤

"23. "ኤቲይል አልኮል" ማለት ጥራቱ 80 ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ አልኮል ነው፤"

"24. "አዲስ ተሽከርካሪ" ማለት ከተመረተበት ዓመት ጀምሮ ከዚህ በታች ከተመለከተው በላይ አገልግሎት ያልሰጠ ተሽከርካሪ ሲሆን፤ የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ. በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠም ሙሉ በሙሉ ተበትኖ ወደአገር የገባ ወይም በከፊል ተበትኖ ወደአገር የገባ ተሽከርካሪ፤

ለ. በጉምሩክ ታሪፍ በአንቀጽ 87.02፣ 87.03፣ 8704፣ 87.05 እና 87.11 የሚመደብ ሆኖ፤ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሞ ወደአገር የገባ፤ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) በደረሰበት ጊዜ የተመረተበትን የዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

በጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ዕድሜው ከሶስት ዓመት የማያልፍ እና ከውጭ አገር እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) ድረስ የተነዳው ርቀት ከ4,000 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ለ" በታሪፍ አንቀጽ ተለይተው ከተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ በሚቆጠር በአራት የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰ ነው::"

"25. *"ያገለገለ ተሽከርካሪ"* ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (24) ለአዲስ ተሽከርካሪ በተሰጠው ትርጉም የማይሸፈን ተሽከርካሪ ሲሆን፤ የአገልግሎት ዘመኑም ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ይጨምራል::"

2. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፤

"2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 በተደነገገው መሰረት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 1 የተዘረዘሩት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በሰንጠረዡ በተመለከተው የማስከፈያ ልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል::"

3. ከአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፤

"(3) ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 1 በተመለከተው በጉምሩክ ታሪፍ ምዕራፍ 15 በሚመደበው የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብና ዘይት እና የእነዚህ ተዋጽዖ ውጤቶች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ መሰብሰብ የሚጀመርበት ቀን ከጤና ሚኒስቴር በሚደርሰው መረጃ መሰረት በገንዘብ ሚኒስቴር ይወሰናል::"

4. የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው ተራ ፊደል (ሀ) ተተክቷል፡

"1. (ሀ) ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 2 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች፤"

5. ከአዋጁ አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተጨምሯል፤

"5. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት የባንክ ፈቃድ አግኝተው ከማናቸውም ቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ዕቃዎች ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ

በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደአገር የሚገቡ ከሆኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይደረጉባቸውም፡፡"

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ ከ______ቀን 2015 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ _____ቀን 2015 ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

| ታሪፍ ቁጥር<br>Tariff Number | የዕቃው ዓይነት | Description | ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ<br>Excise Rate |
|---|---|---|---|
| በምዕራፍ 15 የሚመደቡ | ለምግብነት የተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም የሳቹሬትድ ቅባት መጠኑን ከተለጠፈበት መግለጫ ላይ ለማወቅ የማይቻል የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብና ዘይት እና የእነዚህ ተዋጽዖ ውጤቶች፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሀይድሮጂን የተጨመረበት የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብና ዘይት:: | Edible animal or vegetable fats and oils and their cleavage products; Edible animal or vegetable fats and oils partially or wholly hydrogenated with content of 40g or more saturated fat per 100g or unable to determine level of saturated fat from label.. | 30% |
| 17.01 | ስኳር ለህክምና ከሚውለው በስተቀር | Sugar, excluding of a kind used for medical purpose | 10% |
| 1704.1000 | ማስቲካ | Chewing gum | 10% |
| ከ1704.90 እስከ 1806.90 | በቀጥታ ለምግብነት እንዲውል የተዘጋጀ ቸኮሌት እና ጣፋጭ ከረሜላዎች | Checolate prepared for direct consumption and confectioneries | 10% |
| 2106.9040 | ዱቄት ለስላሳ መጠጦች | Powder soft drinks | 25% |
| 2201.1000<br>2201.9000 | ውሃዎች፣ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ የማዕድን ውሃዎችና ጋዝ ያላቸው ውሃዎች ጭምር፣ ስኳር ወይም ሌላ ማጣፈጫ ያልተጨመረባቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው ያልተደረጉ | Waters, including natural or artificial mineral waters and aerated waters, not containing added sugar or other sweetening matter nor flavored | 10% |
| 2202.1000 | ውሃዎች ማዕድን ውሃዎችና ጋዝ ያላቸው ጭምር ስኳር ወይም ሌላ ማጣፈጫ ያላቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉ | Waters, including mineral waters and aerated waters, containing added sugar or other sweetening matter or flavoured | 25% |
| 2202.9100 | አልኮል አልባ ቢራ የአልኮል ይዞታው ከ0.5 በመቶ ያልበለጠ | Non-alcoholic beer having an alcoholic strength by volume not exceeding 0.5% vol. | 25% |
| 2202.9990 | ውሃ እና ስኳር በመጨመር ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ አልኮል አልባ መጠጦች፣ ስኳር ወይም ሌላ ማጣፈጫ ቢጨመርባቸውም ባይጨመርባቸውም ነገር ግን ከአትክልትና ፍራፍሬ ጭማቂዎች ውጪ፣ በብቅል እንዲፈላ ያልተደረገ፣ ስፕሪት ያልተጨመረበት | Non-alcoholic beverages ready for consumption by the addition of water and sugar and straining, but not include fruit or vegetable juices, unfermented not containing added sprit whether or not containing added sugar or other sweetening matter. | 25% |
| 2203.0000 | ከብቅል የተዘጋጀ ቢራ | Beer made from malt | 40% or 11 Birr per liter, whichever is higher |
| | ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ተመርቶ በበቀለ ገብስ የተመረተ ቢራ | Beer produced exclusively from barley grown and malted in Ethiopia. | 35% or 9 Birr per liter whichever is higher |
| | ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በአገር ውስጥ ግብዓት የተመረተ ቢራ | Beer the local raw material content of which excluding water is at least 75% by weight of its constituents. | 30% or 8 Birr per liter whichever is higher |
| 2204.1000 | ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በአገር ውስጥ ግብዓት የተመረተ የወይን ጠጅ | Wine the local raw material content of which excluding water is at least 75% by weight of its constituents. | 30% |

| ታሪፍ ቁጥር<br>Tariff Number | የዕቃው ዓይነት | Description | ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ<br>Excise Rate |
|---|---|---|---|
| 2204.10 እስከ 2205.90 | ውሃን ሳይጨምር ከክብደቱ ከ75% በታች የሚያህለው የአገር ውስጥ ግብዓት በመጠቀም የተመረተ የወይን-ጠጅ | Wine the local raw material content of which excluding water is at less than 75% by weight of its constituents. | 40% |
| 2206.00 | የሚፈሉ መጠጦች (ሲዳር፣ ፔሪ፣ ሜድ፣ ኦፃክ ቢራ፣ የሩዝ አልኮል መጠጥ)፣ የሚፈሉ መጠጦችና የአልኮል አልባ መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፣ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፣ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ | Fermented beverages (for example, cider, perry, mead, sake, opaque beer), and with mixtures of fermented beverages with non-alcoholic beverages and sprituos beverages and stout and of other beer kind, powdered beer, of an alcoholic content not more than 7% vol | 40% or 11 Birr per liter, whichever is higher |
| | የሚፈሉ መጠጦች (ሲዳር፣ ፔሪ፣ ሜድ፣ ኦፃክ ቢራ፣ የሩዝ አልኮል መጠጥ)፣ የሚፈሉ መጠጦችና የአልኮል አልባ መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፣ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፣ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% የበለጠ | Fermented beverages (for example, cider, perry, mead, sake, opaque beer), and with mixtures of fermented beverages with non-alcoholic beverages and sprituos beverages and stout and of other beer kind, powdered beer, of an alcoholic content more than 7% by volume | 80% |
| 2207.10 እና 2208.9090 | ባሕርዩ ያልተለወጠ ኤቲይል አልኮል | Undenatured ethyl alcohol | 10% |
| ከ2208.20 እስከ 2208.70 | ሲቢርቶዎች፣ ወይን ጠጅን ወይም ግሬፕ ማርክን በማጣራት የሚገኙ፣ ውስኪዎች፣ ከተብላላ የሸንኮራ አገዳ ውጤት በማጣራት የተገኙ ረም እና ሌሎች ስፕሪቶች፣ ጂን እና ጄኔቫ ቮድካ፣ እና ሊክርስና ኮርዲያልስ | Spirits obtained by distilling grape wine or grape marc, Whiskies, Rum and other spirits obtained by distilling fermented sugarcane products, Gin and Geneva, Vodka, and Liqueurs and cordials | 80% |
| 2208.9010 | በድብልቅ የተዘጋጁ፣ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ ጥንካሬ ያላቸው መጠጦች | Ready to drink mixtures of an alcoholic content not exceeding 7% vol | 40% or 11 Birr per liter, whichever is higher |
| 2208.9090 | በይዘታ 7% የበለጠ ነገር ግን ከ80% ያነሰ ጥንካሬ ያለው ሲቢርቶዎች፣ ሊክርስና ሌሎች ሲቢርቶ ያላቸው መጠጦች (ሲቢርቶዎች፣ ወይን ጠጅን ወይም ግሬፕ ማርክን በማጣራት የሚገኙ፣ ውስኪዎች፣ ከተብላላ የሸንኮራ አገዳ ውጤት በማጣራት የተገኙ ረም እና ሌሎች ስፕሪቶች፣ ጂን፣ ጄኔቫ፣ ቮድካ፣ ሊክርስ፣ ኮርዲያልስ እና በድብልቅ የተዘጋጁ አልኮል መጠጦች ሳይጨምር) | Spirits, liqueurs and other spirituous beverages of an alcoholic strength by volume exceeding 7% vol but not exceeding 80% vol (other than spirits obtained by distilling grape wine or grape mar, whiskies, rum and other spirits obtained by distilling fermented sugarcane products, gin, Geneva, vodka, liqueurs, cordials and Ready to drink mixtures) | 80% |
| 2401.1000 | የተቀነጠሰ ትምባሆ | Tobacco, not stemmed/stripped | 20% |
| 2401.2000 | በከፊል ወይም በሙሉ ያልተቀነጠሰ ትምባሆ | Tobacco, partly or wholly stemmed/stripped | 20% |
| 2401.3000 | የትምባሆ ውዳቂ | Tobacco refuse | 20% |
| 2402.1000 | ሲጋሮች፣ ቼሩትስና ሲጋሪሎስ፣ ትምባሆን የያዙ | Cigars, cheroots and cigarillos, containing tobacco | 30% + 250 Birr per Kilogram |
| 2402.2000 | ትምባሆ የያዙ ሲጋራዎች | Cigarettes containing tobacco | 30% + 8 Birr per pack (20 stick) |
| 2402.9000 | እንደ ትምባሆ ሆኖ የሚያገለግሉ የተዘጋጁ ሲጋሮች፣ ቼሩትስና ሲጋሪሎስና ሲጋራዎች | Cigars, cheroots, cigarillos and cigarettes of tobacco substitutes. | 30% + 8 Birr per pack |

| ታሪፍ ቁጥር Tariff Number | የዕቃው ዓይነት | Description | ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ Excise Rate |
|---|---|---|---|
| | | | (20 stick) |
| 2403.1900 | የሚጨስ ትምባሆ፣ በማናቸውም ምጣኔ እንደ ትምባሆ፣ የሚያገለግሉ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም ባይሆንም (የፍራፍሬ ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉም ያልተደረጉም የትምባሆና ግላይሰሮል ቅልቅል የያዘ ትምባሆ ለማጨስ የሚያገለግል በውሃ ማስተላለፊያ ቱቦ የሚጨስ መዓዛ ሰጭ ዘይት እና ምዝግቦች፣ ሞላሰስ ወይም ስኳር ከተጨመረባቸውም ሆነ ካልተጨመረባቸው በስተቀር) | Smoking tobacco, whether or not containing tobacco substitutes in any proportion other than tobacco intended for smoking in a water pipe and which consists of a mixture of tobacco and glycerol, whether or not containing aromatic oils and extracts, molasses or sugar, and whether or not flavoured with fruit. | 30% + 250 Birr per Kilogram |
| 2403.9100 | "የተዋሐደ" ወይም "እንደገና የተዘጋጀ" ትምባሆ | "Homogenised " or "reconstituted" tobacco | 30% + 250 birr per Kilogram |
| 2403.9900 | ሱረት፣ የትምባሆ ምዝግቦችና ኤሰንሶች | Snuff, tobacco extracts and essences | 30% + 250 birr per Kilogram |
| 2501.0010 | ጨው | salt | 10% |
| በምዕራፍ 27 የሚመደቡ | ኬሮሲን፣ ቤንዚን እና ናፍጣ ነዳጆች | Kerosene, Benzene and Diesel Oils | 15% |
| ~~3303.0000~~ | ~~ሽቶዎችና ለስላሳ ሽቶዎች~~ | ~~Perfumes and Toilet Waters~~ | ~~100%~~ |
| 3304.1000 | የከንፈር ቀለም ዝግጅቶች | Lip make-up preparations | 100% |
| 3304.2000 | የዓይን መኳኳያ ዝግጅቶች | Eye make-up preparations | 100% |
| 3304.3000 | የእጅ ወይም የእግር ማሳመሪያ ዝግጅቶች | Manicure or pedicure preparations | 100% |
| 3304.9990 | ግሪስ ፔይንት፣ የቁንጅና ክሬሞች፣ ኮልድ ክሬም፣ መኳኳያ ክሬም፣ ክሊንሲንግ ክሬም፣ የተጨማደደ ቆዳ ማስተካከያ ኢንጀክቱብል ኢንትራኩታኒየስ ጄል፣ ከንፈር ማወፈሪያ (ሃሉሮኒክ አሲድ የያዙትን ጨምሮ) | Grease paints, beauty creams, cold creams, make-up creams, cleansing creams, injectable intracutaneous gels for wrinkle elimination and lip enhancement (including those containing hyaluronic acid) | 100% |
| 3305.2000 | የፀጉር ማለስለሻ ወይም ማከርደጃ ዝግጅቶች | Preparations for permanent waving or straightening of hair | 100% |
| 3305.3000 | የፀጉር ቀለም | Hair lacquers | 100% |
| 3305.9090 | የፀጉር ስፕሬይ፣ ፀጉር እንዲያብረቀርቅ የሚያደርጉ ዝግጅቶች እና የፀጉር ማንጫ ዝግጅቶች | Hair sprays, brilliantines and bleaches | 100% |
| 3604.1000 | ርችቶች | Fireworks | 100% |
| 3923.2110 3923.2910 | ሾፒንግ ፕላስቲክ ባጋ (ፌስታል) | Shoping plastic bags | 40 birr per kg |
| ከ4011.10 እስከ 4013.90 | ጎማዎች | Tyres | 5% |
| ምዕራፍ 50 እስከ 63 ከ57 በስተቀር | ጨርቅ እና ልብስ | Textile and garments | 5% |
| ምዕራፍ 57 | ምንጣፎች፣ ከጨርቃጨርቅ የተሠሩ የወለል መሸፈኛዎች | Carpets and textile floor coverings | 15% |
| 6702.1000 6702.9000 | አርቲፊሻል አበባዎች | Artificial flowers | 10% |

| ታሪፍ ቁጥር Tariff Number | የዕቃው ዓይነት | Description | ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ Excise Rate |
|---|---|---|---|
| ከ6703.00 እስከ 6704.90 | ሀገር | Hair | 40% |
| ከ6811.40 እስከ 6813.20 | አስቤስቶስ | Asbestos | 20% |
| በምዕራፍ 71 የሚመደቡ | ጌጣ ጌጦች | Ornaments | 20% |
| ከ87.01 እስከ 87.02 | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ | Used Vehicles, of age exceeding five years Vehicle | 200% |
| 8703.10 | ያገለገለ፣ በበረዶ ላይ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች የጎልፍ መኪናዎችና ተመሳሳይ ተሽከርካሪዎች | Used Vehicles, Vehicles specially designed for travelling on snow; golf cars and similar vehicles | 200% |
| | የሲሊንደር ይዘቱ ከ1500 ሲ.ሲ. ያልበለጠ ባለ ኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን፣ ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል፣ እና ኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን | Vehicles, including three-wheeler, with only spark-ignition internal combustion reciprocating piston engine, diesel or semi-diese of a cylinder capacity not exceeding 1500 cc | |
| ከ8703.21 እስከ 8703.31 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 10% |
| ከ8703.21 እስከ 8703.31 | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 60% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years Vehicle | 110% |
| | ያገለገለ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding five years Vehicle | 410% |
| | የሲሊንደር ይዘቱ ከ1501-2500 ሲ.ሲ. ባለኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን፣ ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል፣ እና ኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን ተሽከርካሪ | Vehicles, with only spark-ignition internal combustion reciprocating piston engine, diesel or semi-diesel of a cylinder capacity 1501-2500 cc | |
| ከ8703.23 እስከ 8703.32 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 20% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 70% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years Vehicle | 120% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding five years Vehicle | 420% |
| | የሲሊንደር ይዘቱ ከ2501-3000 ሲ.ሲ. ባለኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን፣ ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል፣ እና ኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን ተሽከርካሪ | Vehicles, with only spark-ignition internal combustion reciprocating piston engine, diesel or semi-diesel of a cylinder capacity 2501-3000 cc Vehicle | |
| ከ8703.23 እስከ 8703.33 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 30% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 80% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years Vehicle | 130% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used, of age exceeding five years Vehicle | 430% |

| ታሪፍ ቁጥር Tariff Number | የዕቃው ዓይነት | Description | ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ Excise Rate |
|---|---|---|---|
| | የሲሊንደር ይዞታ ከ3000 ሲሲ. የበለጠ ባለኮምፕሪሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን፣ ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል፣ እና ኮምፕሪሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን ተሽከርካሪ | Vehicles, with only spark-ignition internal combustion reciprocating piston engine, diesel or semi-diesel of a cylinder capacity exceeding 3000 cc | |
| ከ8703.24 እስከ 8703.33 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 40% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 90% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years Vehicle | 140% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding five years Vehicle | 500% |
| | የሲሊንደር ይዞታ ከ1500 ሲሲ. ያልበለጠ ለፕሮፐልሽን የስፓርክ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂንና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረው የያዘ ተሽከርካሪ | Vehicles, with both spark-ignition internal combustion piston engine and electric of a cylinder capacity not exceeding 1500 cc | |
| ከ870340 እስከ 8703.70 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 5% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 60% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years Vehicle | 110% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ | Used Vehicles, Of age exceeding five years Vehicle | 410% |
| | የሲሊንደር ይዞታ ከ1501-2500 ሲሲ. ለፕሮፐልሽን የስፓርክ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂንና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረው የያዘ ተሽከርካሪ | Vehicles, with both spark-ignition internal combustion piston engine and electric of a cylinder capacity 1501-2500 cc | - |
| ከ870340 እስከ 8703.70 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 10% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 70% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years Vehicle | 120% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, Of age exceeding five years Vehicle | 420% |
| | የሲሊንደር ይዞታ ከ2501-3000 ሲሲ. ለፕሮፐልሽን የስፓርክ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂንና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረው የያዘ ተሽከርካሪ | Vehicles, with both spark-ignition internal combustion piston engine and electric of a cylinder capacity 2501-3000 cc | |
| ከ870340 እስከ 8703.70 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 20% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 80% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years Vehicle | 130% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ | Used Vehicles, of age exceeding five years Vehicle | 430% |
| | የሲሊንደር ይዞታ ከ3000 ሲሲ. የበለጠ ለፕሮፐልሽን የስፓርክ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂንና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረው የያዘ ተሽከርካሪ | Vehicles, with both spark-ignition internal combustion piston engine and electric of a cylinder capacity exceeding 3000 cc | - |
| ከ870340 እስከ 8703.70 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 30% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age one year or more but not exceeding two years Vehicle | 90% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከ5 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding two years but not exceeding five years | 140% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding five years Vehicle | 500% |

| ታሪፍ ቁጥር<br>Tariff Number | የዕቃው ዓይነት | Description | ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ<br>Excise Rate |
|---|---|---|---|
| ከ8704.10 እስከ 8704.90 | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding five years Vehicle | 200% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከ5 ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, 0f age exceeding five years Vehicle | 200% |
| ከ8711.10 እስከ 8711.90 | አዲስ ተሽከርካሪ | New Vehicle | 10% |
| | ያገለገለ ተሽከርካሪ፣ ከአንድ ዓመት የበለጠ ተሽከርካሪ | Used Vehicles, of age exceeding one year | 200% |
| 9504.2000 | ሁሉም ዓይነት የቢሊያርድ ዕቃዎችና ተጨማሪ መሣሪያዎች | Articles and accessories for billiards of all kinds | 20% |
| 9504.3000 | በሳንቲሞች፣ በባንክ ኖቶች /በወረቀት ገንዘብ/፣ በባንክ ካርዶች፣ በቶክን ወይም በሌላ ዓይነት የክፍያ ዘዴ የሚሠሩ፣ ሌሎች መጫወቻዎች፣ ከአውቶማቲክ የቦውሊንግ መሣሪያዎች ሌላ | Games, operated by coins, banknotes, bank cards, tokens or by any other means of payment | 20% |
| 9504.4000 | መጫወቻ ካርታዎች | Playing cards | 20% |
| 9504.5000 | ቪዲዮ ጌም ኮንሶሎችና ማሽኖች፣ በንዑስ አንቀጽ 9504.30 ከተጠቀሱት ሌላ | Video game consoles and machines | 20% |
| 9504.9000 | የመዝናኛ ዕቃዎች፣ የጠረጴዛ ወይም የቤት ውስጥ መጫወቻዎች፣ ፒንቴብልስ፣ለካዚኖ ጨዋታዎች የሚያገለግሉ ልዩ ጠረጴዛዎች እና አውቶማቲክ የቦውሊንግ መጫወቻ መሣሪያዎች | Articles for funfair, table or parlour games, including pintables, special tablets for casino games and automatic bowling alley equipment | 20% |
| 9505.1010 | በእጅ የተሠሩ ለገና በአል የሚሆኑ ዕቃዎች | Handmade articles for Christmas festivities | 20% |
| 9505.1090 | በፋብሪካ የተሠሩ ለገና በአል የሚሆኑ ዕቃዎች | Manufactured articles for Christmas festivities | 20% |
| 9505.9000 | የበአል፣ የካርኒቫል ወይም ሌሎች የማስተናገጃ ዕቃዎች፣ የአስማት መጫወቻዎችና መቀለጃዎች ጭምር | Festive, carnival or other entertainment articles, including conjuring tricks and novelty jokes | 20% |

## የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች

| የአገልግሎቱ ዓይነት | Description | የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ<br>Excise Rate |
|---|---|---|
| የሞባይል አገልግሎቶች (ኢንተርኔት፣ የድምፅ እና የፅሑፍ መልክት)፣ የገመድ አልባ ስልክ አገልግሎት፣ የገመድም ሆነ ገመድ አልባ የኢንተርኔት አገልግሎቶች | Telecommunication service of mobile and wireless telephone (Internet, Voice and SMS) | 5% |

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድና አስተዳደር አገልግሎት 2



በኢትዮጵያ ... Ethiopian ... Record ... No. 2

## ሠንጠረዥ ሁለት

### ክፍል አንድ
### ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

1. አውሮፕላን በዓለምዐቀፍ ትራፊክ እንቅስቃሴ ውስጥ ባለበት ጊዜ ተሳፋሪ መንገደኞች እና የአውሮፕላኑ ሠራተኞች በጉዞ ወቅት የሚጠቀሙባቸው በነፃ የሚሰጡ ዕቃዎች፣

2. የዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ የዲፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዟቸው በዲፕሎማቶች መብትና ጥቅም ደንብ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

3. በመንግሥት ጥሪ መሰረት በአደጋ የተጐዱ ሰዎችን ለመርዳ እንዲውሉ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች፣

4. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ወይም የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙዋቸው በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

5. ከተሽከርካሪ በስተቀር ወደአገር የሚገቡ መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡ አግባብ ባለው ሕግ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፤

### ክፍል ሁለት
### ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ አገልግሎቶች

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፤

- ለዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ የዲፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች የሚሰጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች፤

**PROCLAMATION NO_____/2023**

**EXCISE TAX (AMENDMENT) PROCLAMATION**

**WHEREAS**, it has become necessary to lower the exaggerated excise tax rate imposed on imported new vehicles and some other items;

**WHEREAS**, it is found not proper to grant persons and organizations with special tax and duty privileges to also import goods on which excise tax is imposed because of the damage they inflict on the environment free of excise tax;

**WHEREAS**, it is believed that imposing excise tax on telecommunication services will help generate more revenue to finance development activities carried out by the Government;

**NOW THERFORE**, in accordance with Article 55(1) of Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Excise Tax (Amendment) Proclamation No. ___/2023".

**2. Amendment**

The Excise Tax Proclamation No.1186/2020 (as amended) is hereby further amended as follows:

1. The following new sub-articles (23), (24) and (25) are added after sub-article (22) of Article 2 and the existing sub-articles (23)-(34) are renumbered from (26)-(37) respectively:

"23. "**Ethyl alcohol**" means alcohol of purity of 80 degrees or more;"

"24. "**New Vehicle**" means a vehicle that has not been used over what is stated in this sub-article since its manufacturing year and includes the following:

a. imported in semi-knocked Down (SKD) or Complete Knocked Down (CKD) form to be assembled by local industry ;

b. a Complete Built Up (CBU) vehicle of tariff heading 87.02, 87.03, 87.04, 87.05 and 87.11 which arrives at the Ethiopian customs territory (entry point) within a time period of three Gregorian calendar years including the manufacturing calendar year of the vehicle and when the number of kilometers driven abroad at the time it arrives at the Ethiopian custom territory (entry point) does not exceed 4,000 kilometers;

c. If the vehicle is not covered under sub-letter (b) of this sub-article it arrives at Ethiopian custom territory (entry point) within a time period of four Gregorian calendar years including the manufacturing calendar year of the vehicle;"

"25. " **Used Vehicle**" means a vehicle not covered under sub-article 24 of this Article and the age is counted beginning the manufacturing Gregorian calendar year to the Gregorian calendar year of its arrival at Ethiopian customs territory (entry point);"

2. Sub-Article (2) Article 5 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article 2:

   "2. Excise Tax shall be charged at the rate specified in the first Schedule 1 attached herewith for the excisable goods and services in force at the time the liability arises for excise tax as determined under Article 9 of this Proclamation."

3. The following new sub-article (3) is added after sub-article (2) of Article (5) of this Proclamation:

   "(3) The commencement date for collection of excise tax charged on edible animal or vegetable fats and oils and their cleavage products specified in Schedule 1 attached herewith as classified in Chapter 15 of the Customs Tariff shall be determined by the Ministry of Finance based on the information it receives from the Ministry of Health."

4. Sub-article 1 (a) of Article 8 is deleted and replaced by the following new "a':

   "a. exempt goods which meet the conditions set out under the Second Schedule attached with this Proclamation;"

5. The following new sub-article (5) is added after sub-article (4) of Article 43

   " 5. Excise tax on goods to be imported into Ethiopia free of any taxes and duties, for which bank permit has been obtained prior to the enactment of this Proclamation and imported within two months from the effective date of this Proclamation shall be assessed and collected in accordance with the Excise Tax Proclamation No.1186/2020 (as amended)."

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on this ____day of _______2023.

Done at Addis Ababa this ____day of ____2023.

SAHLEWORK ZEWDE
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## SECOND SCHEDULE
## PART A

## EXEMPT EXCISABLE GOODS

The following excisable goods shall be exempt from excise duty:

1. Excisable goods that are bona fide stores for aircraft, being goods for use or consumption by passengers or crew of aircraft while on board and while the aircraft is in international traffic;
2. Excisable goods imported into Ethiopia or purchased in Ethiopia by a diplomatic or consular mission, or by a diplomat or consul, or a member of the diplomat or consul's family forming part of the diplomat or consul's household in Ethiopia to the extent provided for under the Privileges and Immunities Regulations;
3. imported consignments for emergency relief in response to an emergency call issued by the Government;
4. All goods imported or purchased locally for the official use by the Ethiopian Defense Forces and the Federal and State Police Commissions as provided in a Directive issued by the Minister;
5. Excisable goods except vehicle imported by, and in the possession of a passenger subject to limitations provided for in the appropriate law.

## PART B
## EXEMPT EXCISABLE SERVICES

The following excisable services shall be exempt from excise duty:

- Excisable services supplied in Ethiopia to a diplomatic or consular mission or to a diplomat or consul, or a member of the diplomat or consul's family forming part of the diplomat or consul's household in Ethiopia to the extent provided for under the Privileges and Immunities Regulations.